በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን

# የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት




ነሐሴ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


1. መግቢያ ---------------------------------------------------------------- 1

2. የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አደረጃጀት---------------------------------3

2.1 የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት-------------------3

2.2 የክልል ሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላት------------------------------4

2.3 የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነ---------- 5

2.4 የክልል የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት-----------6

3. የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርናኃላፊነት------------------------------------------------------- --9

3.1 የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ አባላት----------------------------------------------------1,0

## 1. መግቢያ

የሕዝብ ቆጠራ ሥራን በህዝቡ ሙሉ ድጋፍና ትብብር በታቀደለት ጊዜ ለማካሄድ እንዲቻል በቆጠራው ሂደት የሚመራ የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን እና የኮሚሽን ጽ/ቤት እንዲሁም በክልል በሚገኙ የአስተዳደር መዋቅሮችን በመከተል ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ይቋቋማሉ።

በሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ከማዕከል እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የሚቋቋሙ ኮሚሽኖችና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ኮሚቴዎች የተጣለባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ እንዲያውቁትና የአፈጻጸም ክትትል ለማድረግ እንዲቻል ከየሥራ ዘርፎች ድርጅታዊ መዋቅር ጋር ተስማሚ የሆነ የተግባርና ሃላፊነት መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በየደረጃው ከክልል እስከ ወረዳ የተቋቋሙ የቆጠራ የሥራ ዘርፎችና በየደረጃው በአመራር ላይ የተመደቡ ኃላፊዎች ለሚያከናውኑት የቴክኒክና የአስተዳደር ስራዎች እንዲሁም የቆጠራውን ዓላማ ለማስፈጸም በሥራ ላይ ለሚያውሉት የሰው ኃይልና ማቴሪያል ግልጽ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የዘመቻ መልክ ያለው ሲሆን በየደረጃው በሚቋቋሙት ኮሚሽኖች መዋቅር መሠረት በየኮሚሽኑ ጽ/ቤቶች የጽ/ቤት ኃላፊ እና የመስክ ሥራ አስተባባሪ ከአገር አቀፍ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የሚመደብ ሲሆን ሌሎች ድጋፍ ሰጪ የሰው ኃይል ግን ከየአስተዳደር እርከኑ የመንግስት መ/ቤቶች በሚመደብ የሰው ኃይል የሚሟላ ይሆናል።

በሕዝብና ቤት ቆጠራ እንቅስቃሴ ወቅት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች የሥራ አፈጻጸም፣ የክትትልና የሪፖርት አቀራረብ ነው።

በየደረጃው የሚዋቀሩ የኮሚሽን ጽ/ቤቶችና ኃላፊዎች ለቆጠራው ሥራ የወጡ መመሪያዎችን ተከትለው ሥራዎችን በወቅቱ በማከናወን ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውንና የአፈጻጸም መመሪያዎች በትክክል በሥራ መተርጎማቸውን የመከታተሉ ጉዳይ ትኩረት የሚደረግበት ይሆናል። የሕዝብና ቤት ቆጠራ የዝግጅት ሥራዎችና ዋናው ቆጠራ በተወሰነ ቀን ተጀምሮ በተወሰነ ቀን የግድ ማለቅ የሚገባው ተግባር ከመሆኑም ባሻገር የአንዱ ሥራ መጓተት ለሌላው እንቅፋት እንደሚሆን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በየደረጃው የሚዋቀሩ ኮሚሽኖች የበላይ አመራሮች ለቆጠራው ቅድሚያ በመስጠት የሥራ ፕሮግራሞችና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በተቻለ ፍጥነት በተግባር መተርጎም ይኖርባቸዋል። ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ የኮሚሽን ሰብሳቢና አባላት እንዲሁም የጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በሥራ አፈጻጸም ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በአፋጣኝ መፍታት እንዲሁም ከአቅም በላይ የሆኑትን ምቹ በሆነው መንገድ ሪፖርት የማቅረብ፣ የሚከሰቱ ችግሮች ሁሉ መልስ ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

ሌላው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ምልመላ ሲሆን ከአገር አቀፉ የኮሚሽን ጽ/ቤት በሚተላለፈው አንድ ወጥ የሆነ መመዘኛ መሠረት ብቁ የሆኑት በየደረጃው ባሉ የኮሚሽኑ አባል መ/ቤቶችና በቆጠራ ጽ/ቤቶች አማካኝነት እንዲመለመሉ ይደረጋል። ይህ ሂደት በትክክል መፈጸሙን በየደረጃው ያሉ ኮሚሽኖች ክትትል ያደርጋሉ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታሉ።

የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ካበቃ በኋላ ወደ ምድብ ቦታቸው የማድረስ ሥራ አንድ ጊዜ ሊከናወን የሚገባውና ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መከናወን ይገባዋል። በክልልደረጃ የሚቋቋመውየሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንና

እንዲሁም የየኮሚሽኑ ስብሳቢና ፀሐፊ ከላይ የተጠቀሱት ዋና ጉዳዮችን ጨምሮ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል።

## 2. የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አደረጃጀት

### 2.1 የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት

የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለአገር አቀፉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. ከአገር አቀፉ ኮሚሽን የተላለፉ መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

ለ. ለቆጠራው ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም በክልሉ ውስጥ ለሚገኘው ሕዝብ እንዲሁም መ/ቤቶችና ድርጅቶችን ተገቢው ቅስቀሳና የማስተባበር ሥራ መከናወኑን ይከታተላል፣

ሐ. የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም ስልቶችን ይቀይሳል፣

መ. ለክልሉ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ማስፈጸሚያ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል፣ የገንዘብ፣ የማቴሪያል፣ የትራንስፖርትና ሌሎች ቁሳቁሶች መሟላታቸውንና አፈጻጸማቸውን ያረጋግጣል፣

ሠ. የቆጠራውን ሥራ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን በሚወሰነው ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፣

ረ. ከሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን በሚተላለፍ መመሪያ መሰረት በክልሉ በየደረጃው የሕዝብ ቆጠራ አስፈጻሚ አካላትን ያደራጃል፡፡

ከዞን/ከወረዳ ሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሰ. በክልሉ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የተመደበው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል የሚቀርብለትን የኦዲት ሪፖርት አጽድቆ ለአገር አቀፉ ኮሚሽን ያቀርባል፣

## 2.2 የክልል ሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላት

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ክልሉን በመወከል የአገር አቀፉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባል | ሰብሳቢ |
| 2 | የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 3 | የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ | አባል |
| 4 | የከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 5 | የትምህርት ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 6 | የጤና ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 7 | የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 8 | የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች /የፖሊስ ኮሚሽን/ ኃላፊ | አባል |
| 9 | የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 10 | የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 11 | የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 12 | የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 13 | የሥነ-ሕዝብ ቢሮ ወይም መምሪያ ኃላፊ | አባል |
| 14 | የማዕከላዊ ኤጀንሲ የሚመደብ የክልሉ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ | አባልና ፀሐፊ |

ማስታወሻ፡-

የኮሚሽኑ አባላት ስብጥር እንደየክልሉ የአደረጃጀት ሁኔታ ሊለያይ ይችላል።

## 2.3 የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

የብሄራዊ ክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለአገር አቀፉ ሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

ሀ. የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላትን እንደአስፈላጊነቱ ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውን በሰብሳቢነት የመምራትና የተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር መተርጎማቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣

ለ. ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም በክልሉ ለሚገኘው ሕዝብ እንዲሁም መ/ቤቶችና ድርጅቶች በቂ ቅስቀሳ መካሄዱን ማረጋገጥ፣

ሐ. የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በመሆን ስልቶችን መቀየስ፣

መ. በክልሉ በዋናው ቆጠራ ወቅት ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል፣ የገንዘብ፣ የማቴሪያል፣ የትራንስፖርትና ሌሎች ቁሳቁሶች መሟላታቸውንና አፈጻጸማቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣

ሠ. የቆጠራው ሥራ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን በሚወስነው ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

ረ. ከዞን/ወረዳ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የሚቀርቡ ጉዳዮችን ለክልሉ ኮሚሽን አባላት በማቅረብ ማስወሰንና አፈጻጸሙን መከታተል፣

ሰ. በቆጠራው ሥራ የሚሳተፉና የሚያስተባብሩ ኃለፊዎችንና መምሪት፣ ማስተባበርና መቆጣጠር፣

ሸ. በክልሉ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ችግሮችን አፋጣኝ መፍትሄ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

ቀ. ከአገር አቀፉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የሚተላለፉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፣

በ. የሕዝብ ቆጠራ ሥራን በሚመለከት የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሥራ እንቅስቃሴን በበላይነት መቆጣጠር፡፡

2.4. <u>የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ኃላፊ (ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሚመደብ ሆኖ) ተጠሪነቱ ለክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል፡፡

ሀ. በሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለሕዝብ ቆጠራ ተግባር የተዘጋጁ ልዩ ልዩ የአፈጻጸም መመሪያዎች በየደረጃው ለሚገኙ የቆጠራ ሠራተኞችና ኃላፊዎች መድረሱንና አስፈላጊ ማብራሪያ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣

ለ. ከሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት በሚተላለፍ የድርጊት ፕሮግራም ወይም የጊዜ ሠንጠረዥ መሰረት የተቆጣጣሪዎችና ቆጣሪዎች ምልመላ መከናወኑንና የሥልጠና ቦታ መዘጋጀቱን ይከታተላል፣ እንዲሁም አሰልጣኞች መመደባቸውን ያረጋግጣል፣

የሚሰጠውን ሥልጠና ምደባና ስምሪት ይቆጣጠራል፣

ሐ. በክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሥር የሚገኙትን የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ብዛትና ዝርዝር ማወቅና በቆጠራው መሸፈናቸውን ማረጋገጥ፣

መ. በቆጠራ ካርታ ሥራ ያልተሸፈኑ አካባቢዎችን በሚመለከት ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት በሚተላለፍ መመሪያ መሰረት የቆጠራውን ሥራ ማከናወን፣

ሠ. ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚውሉ መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ የቆጠራ ካርታዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች በቀረበው ዝርዝር መሰረት መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ፣

ረ. ለቆጠራው ሥራ የሚያስፈልግ የሎጂስቲክስ ድጋፍና ማጓጓዣ አገልግሎት ተሟልቶ መገኘቱን ማረጋገጥ፣ ስምሪቱንም ማስተባበርና በበላይነት መቆጣጠር፣

ሰ. የሕዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ ግቡን እንዲመታ በቆጠራው ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞችን የሥራ አፈጻጸም መከታተል፣ ማስተባበርና መቆጣጠር፣ እንዲሁም ከቆጠራው ፍጻሜ በኋላ ሠራተኞችን በአግባቡ ማሰናበት፣

ሸ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ እንቅስቃሴን በሚመለከት ለአካባቢው ህብረተሰብ በቂ ትምህርትና ቅስቀሳ መካሄዱን ማረጋገጥ፣

ቀ. የሕዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ ኮሚሽኑ በሚወስነው ቀን፣ ወር ዓመት ምህረት መሰረት መካሄዱን ማረጋገጥ፣

በ. በዋናው ቆጠራ ጊዜ ለክልሉ የተመደበውን የቆጠራ በጀት ከክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ ጋር በጋራ ማስተዳደር፣ ወጪዎችን መፍቀድ ትክክለኛ የሂሳብ አሰራርና የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት መቋቋሙን፣ ለቆጠራው እንቅስቃሴ የተመደበው በጀት በትክክል ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር መዋሉን፣ ከቆጠራው ፍጻሜ በኋላም በቆጠራው ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ የወጭ ማስረጃ ተሰብስቦ በክልል ኮሚሽን ሂሳቡ መዘጋቱን ማረጋገጥ፣

ተ. በቆጠራው ሥራ ላይ ለተሰማሩ የመስክ ሠራተኞች ምግብ፣ መጠለያ፣ የመንገድ መሪ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጥበቃ አገልግሎት፣ ወዘተ ተሟልቶ መገኘቱን ማረጋገጥ፣

ቸ. በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና ፋይናንስ ረገድ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ችግሮች ከክልሉ ኮሚሽን ሰብሳቢ ጋር በመሆን አፋጣኝ መፍትሄ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

ኀ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ እንደተጠናቀቀ መረጃ የተሞላባቸው መረጃዎች፣ ታብሌቶች፣ መጠይቆችና ቅጾች /ምስጢራቸውን በመጠበቅ/፣ ያልተሰራባቸው ቅጾች፣ የአፈጻጸም መመሪያዎች፣ መታወቂያ ወረቀቶች፣ ሌሎች ቋሚ ዕቃዎች፣...ወዘተ በጥንቃቄ ተሰብስበው ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት መተላለፋቸውን ማረጋገጥ፣

ነ. ከክልሉ ቆጠራ ኮሚሽን የሚሰጠውን መመሪያ በተግባር ማዋልና በተዋረድም መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

ኘ. የክልሉን የሕዝብ ቆጠራ የሥራ ክንውን ሁኔታ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት ከቆጠራው ፍጻሜ በኋላ ለኮሚሽኑ ማቅረብ፣

ለ. ከአገር አቀፍ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት (የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ) የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እየተወጣ ከክልሉ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

3. <u>የክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፤</u>

የብሔራዊ ክልል የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ እንቅስቃሴን በሚመለከት የድርጅቶችና የሕብረተሰቡን ድጋፍና ትብብር ለማግኘት ከማዕከል በሚተላለፍለት መመሪያ መሰረት አስፈላጊውን የቅስቀሳ ፕሮግራም በማዘጋጀት እንዲሁም በወጣው ፕሮግራም መሰረት ማስፈጸም፣

ለ. በቆጠራው ወቅት ከህብረተሰቡ ለሚቀርብለት ጥያቄ ሁሉ ትክክለኛና የተሟላ መልስ ለመስጠት እንዲችል ከብሔራዊ ኮሚቴው በሚተላለፍለት መመሪያ መሰረት ስለሕዝብ ቆጠራ አስፈላጊውን ትምህርት በቃለ መጠይቅ፣ በድራማ፣ በውይይት…ወዘተ መልክ ማሰራጨት፣

ሐ. በብሄራዊ ክልሉ ውስጥ ስለሚካሄደው የሕዝብ ቆጠራ እንቅስቃሴ እንደአስፈላጊነቱ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መግለጫ መስጠት፣

መ. ለሕዝብ ቆጠራ ስኬት የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የተዘጋጁ ጽሁፎችንና ፖስተሮችን በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት እንዲሰራጭ ማድረግ፣

ሠ. በክልሉ ስለሚካሄደው የሕዝብ ቆጠራ ከድርጅቶችና ከግለሰቦች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር አስፈላጊውን መልስ መስጠት፣

ረ. በዞን አስተዳደር ደረጃ ለተቋቋመው ለትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ከማዕከል የሚተላለፉ መመሪያዎችና ዶክመንቶች በትክክል መድረሳቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

ሰ. በተጨማሪም ከብሄራዊ ክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፣

## 3.1. የብሔራዊ ክልል የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የክልል የኮምኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ | ሰብሳቢ |
| 2 | የትምህርት ቢሮ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 3 | የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 4 | የከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 5 | የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 6 | የአካባቢ ጥበቃና ገጠር መሬት አጠቃቀም ባ/ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 7 | የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ኮምኒኬሽን ኃላፊ | አባል |
| 8 | የሃይማኖት ድርጅቶች ተጠሪዎች | አባል |
| 9 | የሕዝባዊ ድርጅቶች ተጠሪዎች | አባል |
| 10 | የክልሉ የሥነ-ሕዝብ መምሪያ ተጠሪ | አባል |
| 11 | ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሚመደበው ቴክኒክ ኃላፊ | አባልና ፀሐፊ |

ማስታወሻ፡-

የቅስቀሳ ኮሚቴው አባላት ስብጥር እንደየክልሉ የአደረጃጀት ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል።